**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

1ki Diro Kiiro 13

Hawaasa, Badheessa 20, 2013 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
ሀዋሳ መጋቢት ፳ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም

**Amado**

**Wodhote Kiiro 13/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Doogote Latishshi Handaari Manaado Kontirakitere woy Amaalaancho Maamarra Tantanate Wodho ………………… Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፲፫/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በመንገድ ልማት ዘርፍ የአነስተኛ ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበራት ማደራጃ ደንብ ………… ገጽ…**

**Wodhote Kiiro 13/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Doogote Latishshi Handaari Manaado Kontirakitere woy Amaalaancho Maamarra Tantanate Wodho**

Doogote xintu latishshi gobbate ikonoome lophora nooha lowo qeecha ammanatenni,

Qoqqowu mootimma doogote tuqishshanna deerra woyyeessate 10 dirita massagaancho latishshu mixo qixxeessatenni loosu giddora e'inoha ikkinohura,

Wole widoonni loosu kaayyo kalaqate baxxino illacha tugatenni babbaxxitino rosu uurrinshubbanni

**ደንብ ቁጥር ፲፫/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በመንገድ ልማት ዘርፍ የአነስተኛ ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበራት ማደራጃ ደንብ**

የመንገድ መሰረተ ልማት ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ያለዉን ከፍተኛ ሚና በማመን፣

የክልሉ መንግስት የመንገድ ሽፋንና ደረጃ ለማሻሻል የ፲ ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ የተሸጋገረ በመሆኑ፣

በሌላ በኩል ለስራ ዕድል ፈጠራ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት

**Mittu Waagi ….**
ያንዱ ዋጋ

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

maassante fultanno wedellootira loosu kaayyo kalaqate widoonni haja la'annonsa bissa ledo qinaawatenni, tantanantino wedellira hasiisanno qajeelsha injeessineenna loosu kaayyo kalaqantannonsa gede hedatenni haaro kontirakiterenna amaalaancho maamarra hattono dooggate biilloonyi hunda loosantanno doogotenna buusu loossa aana noo manaado isitiraakicherubba, ijaarsanna care tuqisate loossa loosa dandiitannota ikkitinota ammannoonnihura,

Qoqqowu deerrinni doogote latishshi loosira beeqitanno manaada kontirakitere woy amaalaancho maamarra tantano, xaphooma loosu beeqooshshe harunsatenna gashshate kaa'lanno seeru qixxeessa hasiisanohura,

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaanote Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 57(6) hunda uynoonnisi biilloonyi garinni tenne wodho fushshino.

## GAFA MITE

## Xaphooma Woro

1. **Harancho Umo**

   Tinne wodho "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Doogote Latishshi Handaari Manaado Kontirakitere woy Amaalaancho Maamarra Tantanate Wodho kiiro 13/2013" yine xawisate dandiinanni.

ተመርቀው ለሚወጡ ወጣቶች የስራ ዕድል ከመፍጠር አንፃር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ለተደራጁ ወጣቶች አስፈላጊውን ስልጠና ተመቻችቶላቸው ስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው በማሰብ አዳዲስ ተቋራጭና አማካሪ ማኅበራትን እንዲሁም በመንገዶች ባለሥልጣን ስር በሚሰሩ የመንገድና ድልድይ ስራዎች ላይ የሚገኙ አነስተኛ ስትራክቸሮች፣ ግንባታና ጠጠር የማመላለስ ስራዎችን መስራት የሚችሉ መሆኑ ስለታመነበት፣

በክልል ደረጃ በመንገድ ልማት ሥራ ላይ የሚሳተፉ አነስተኛ ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበራት አደረጃጀት፣ አጠቃላይ የሥራ ተሳትፎ ለመከታተልና ለማስተዳደር የሚረዳ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፯(፮) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህንን ደንብ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በመንገድ ልማት ዘርፍ የአነስተኛ ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበራት ማደራጃ ደንብ ቁጥር ፲፫/፳፻፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. Tiro

Qaalu horo wole tiro uytannota ikka hoogguro tenne wodho giddo:

1. **“Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
2. **“Olluu Tuqishshi Doogo Ijaarsi Pirograame”** yaa baalanta olluubba insa insawana qara doogga ledo hawado arro horo uytannonna dooggate marawe xaadisate doogote latishshi pirograammeti.
3. **“Madawanya Doogote Ijaarsa”** yaa qoqqowu dooggate biilloonyinni ijaarsinannita, hawadonna arro horo uytannota, deerrase agadhitinota, worada woradunninna qoqqowunni hattono qara doogga ledo xaadissanno doogote marawe diriirsate doogote latishshaati.
4. **“Doogote Gatamarsha”** yaa olluu tuqishshi doogo ijaarsu pirogiraamenni ijaarsineenna dagate seeda yannara horo uytanni ba’ino doogo ijaarsatenni noowa qolate loonsanni gatamarshu loosoti.
5. **“Manaado Kontirakitere woy Amaalaancho Maamara”** yaa Yuuraappete pirogiraame aana beeqqate worroonni bikaano wonshe hajo la’annosi bisinni seeru garinni manaado loosu amaalaanchimmanna kontirakiterimma taje uynoonnisi bisooti.
6. **“Kontirakiterichu woy Amaalaanchu Deerra”** yaa Quchumu Latishshinna Minnate Biiro doogote ijaarsanna manaado

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው::
2. **“የቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ ፕሮግራም”** ማለት ሁሉንም ቀበሌዎች እርስ በእርስና ከዋና መንገዶች ጋር ክረምት ከበጋ በሚያገለግልና የመንገድ መረብ የማገናኘት የመንገድ ልማት ፕሮግራም ነው፡፡
3. **“መደበኛ መንገድ ግንባታ”** ማለት በክልሉ መንገዶች ባለሥልጣን የሚገነባ ክረምትና በጋ የሚያገለግልና ደረጃውን የጠበቀ፣ ወረዳን ከወረዳና ክልል እንዲሁም ከዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኝ የመንገድ መረብ ዝርጋታ የመንገድ ልማት ነው፡፡
4. **“የመንገድ ጥገና”** ማለት በቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ ፕሮግራም ተገንብቶ ለኅብረተሰቡ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት እየሰጠ የተበላሸውን መንገድ በመጠገን ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚሰራ የጥገና ስራ ነው፡፡
5. **“አነስተኛ የሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበር”** ማለት በዩራፕ ፕሮግራም ለመሳተፍ የተቀመጡትን መስፈርቶች በማሟላት በሚመለከተው አካል የአነስተኛ ሥራ አማካሪነትና ተቋራጭነት ሕጋዊ የምስክር ወረቀት የተሰጠው አካል ነው፡፡
6. **“የሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ደረጃ”** ማለት በከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ በመንገድ ግምባታና አነስተኛ ስትራክቸር ስራ ላይ ለሚሳተፉ የሚሰጥ የሥራ ተቋራጭ እና

isitiraakichere loosi aana beeqqitannorira uynanni kontirakiterichinna amaalaanchi deerraati.

7. **“Pirojekitete Bikka”** yaa manaado kontirakiterechi woy amaalaanchi diru dirunku loosate (ijaarsate) dandaannota kiilomeetiretenni bikkinanni doogote seendilli bikkaati.
8. **“Manaada Isitiraakichere”** yaa doogo ijaarsate pirojekitubba giddo tubbo loosa, kaliveritenna fordete.
9. **“Isitiraakichere”** yaa doogote ijaarsa pirojekitubba aana 6 meetirenni – 20 meetire geeshsha seendillu noonsa buussaati.
10. **“Borreessanno Biso”** yaa tenne wodho garinni borreessantanno ku’laano, ku’laatonna taje haa’ratenninna buuxatenni seeru mannimma aate biilloonye uynoonni bisooti.
11. **“Biiro”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma doogote latishshinna hodhishshu biirooti.
12. **“Mancho”** yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannimmate qoosso uynoonnisi bisooti.

**3. Koo-teemmate Xawishsha**

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni xawinsoonnihu hasiishshu garinni wole koo-teemmano amadannoho.

**4. Jeefishshi Mami-Geeshsha**

Tini wodho manaadu kontirakiteremmate woy amalaanchimmate looso loosanno maamari hattono

አማካሪ ደረጃ ነው፡፡

7. **“የፕሮጀክት መጠን”** ማለት የአነስተኛ ሥራ ተቋራጩ ወይም አማካሪው በየዓመቱ ሊያከናውን (ሊገነባ) የሚችለው በኪሎ ሜትር የሚለካ የመንገድ ርዝመት መጠን ነው፡፡
8. **“አነስተኛ ስትራክቸር”** ማለት በመንገድ ግምባታ ፕሮጀክቶች ላይ ቱቦ ቀበራ፣ ካልቨርቶችና ፎርዶች ናቸው፡፡
9. **“ስትራክቸር”** ማለት በመንገድ ግምባታ ፕሮጀክቶች ላይ ከ6 ሜትር - 20 ሜትር ርዝመት ያላቸው ድልድዮች ናቸው፡፡
10. **“መዝጋቢ አካል”** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የሚመዘገቡ አመልካቾችን፣ ማመልከቻዎችንና መረጃዎችን በመቀበልና በመመርመር ሕጋዊ ሰውነት እንዲሰጥ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡
11. **“ቢሮ”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፡፡
12. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**3. የፆታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በአንድ ፆታ የተገለፀው እንደ አግባብነቱ ሌላውንም ፆታ ያካትታል፡፡

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በአነስተኛ የሥራ ተቋራጭነት ወይም አማካሪነት ሥራ ላይ በተሰማራ ማኅበር እንዲሁም ይህንን በሚያስፈጽሙ አካላት ላይ

konne jeefisanno bissa iima jeefishshu noote.

## GAFA LAME

**Manaado Kontirakitere Woy Amalaancho Maamara Uurrisa**

**5. Uurrisate Bikaancho**

Mittu maamari tenne wodho garinni uynanniha seeru mannimma afi’rate tenne wodho quwa 6 hunda worroonniha maamaru miili ogeeyyenni xa’minanni bikaancho hattono miillate ogeeyye ikkado assate uynanni qajeelsha adhite balaxote ikkito wonsha noonsa.

**6. Maamaru Miilla Ogeeyye Rosu Deerra, Loosu Rosichonna Ogimmate Waaxo**

Mitto maamara uurrisate hasiissano ogeeyye ogimmate waaxo, rosu qixxaawo, loosu rosichinna batinyu konni worooni xawinsoonni garinni ikkano:

1. Tenne pirogiraamera doorante beeqqaano ikkitanno ogeeyye wonsha hasiissannonsa rosu qixxaawonna loosu rosicho tenne wodho ledo amadisiisantino shae 1 kayise 3 iima xawinsoonni garinni ikke mittu mittunku maamari ajanni ajenna 6 miilla hanqafinoha ikkanno;
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 garinni tenne wodho ledo amadisiisantino shae 1 nna 2 iima woroonni mannu woliqqa aana mittu mittu



ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

**የአነስተኛ ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኀበር ስለ ማቋቋም**

**5. የማቋቋሚያ መሥፈርቶች**

አንድ ማኅበር በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጠውን ህጋዊ ሰዉነት ለማግኘት በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ሥር የተመለከቱትን ከማኅበሩ አባል ባለሙያዎች የሚጠየቀውን መስፈርት እንዲሁም የአባላቱ ባለሙያዎችን ለማብቃት የሚሰጠውን ሥልጠና በመውሰድ ቅድመ ሁኔታውን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

**6. የማኅበር አባል ባለሙያዎች የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና የሙያ ስብጥር**

አንድ ማኅበር ለማቋቋም የሚያስፈልጉ የባለሙያዎች የሙያ ስብጥር፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ እና ብዛት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡-

1. ለዚህ ፕሮግራም ተመርጠው የሚሳተፉ ባለሙያዎች ማሟላት የሚገባቸው የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረጉ ከሠንጠረዥ 1-3 ላይ በተመለከተው መሠረት ሲሆን እያንዳንዱ ማህበር ቢያንስ 6 አባላት ያቀፈ ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው በሠንጠረዥ 1

tantanamanno maamari hundassiini 25-30 ikkitano mannu woliqqa qaxarano;

3. Konni quwi cinaanchu quwi 1 garinni tenne wodho ledo amadisiisantino shae 3 xawinsonihu amallaanote maamari loosu ogimma xa’manoha ikkinohura jeefishshu manuwaale biirotenni qixxaabbanno;
4. Mittu manaadu loosi amaalaaanchimmatenna kontiraakiterimmate maamari loosoho hassiisanota wole ledote mannu woliqqa qaxadhateni wonshshira dandaano.

## 7. Qajeelshu Beeqqo

1. Manaada kontirakiterimmatenna amaalaanchimmate maamarrara uynanni qajeelshi amado doogote handaari xaphoomunna baxxino garinni olluu tuqishshi doogonna madawanya doogote loosinna manaadonna mereerima isitiraakkicherubba ijaarsate loosi aana ogeeyyete dandoo lossitanno ogimmate hajubba aana illachishannoha ikkanno. Tittirsha biddissunni xawinsanni.
2. Tenne wodho quwa 5 worroonnihu noo gedeenni hee’renna maamaru miillara uynanni qajeelshubba qarunni Qoqqowu Tekiniketenna Ogimmate Qajeelshinna Sayinsenna Tekinolojete Biiro widoonni uynanniha ikkanna Doogote Latishshinna Hodhishshu Biiro shiqqe ha’ruunsanna hasiisi garinni

እና 2 ከተጠቀሰው የሰው ኃይል በተጨማሪ እያንዳንዱ ማህበር በስሩ ከ25-30 ሠራተኛ ይቀጥራል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው በሠንጠረዥ 3 የተጠቀሰው አማካሪ ማህበር ስራ ልምድ የሚጠይቅ ሰለሆነ የአፈፃፀም ማኑዋል በቢሮው ይዘጋጃል፤
4. አንድ የአነስተኛ ሥራ አማካሪና ተቋራጭ ማህበር ለአንድ ማህበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተጨማሪ ባለሙያዎችን በቅጥር ሊያሟላ ይችላል፡፡

## 7. የሥልጠና ተሳትፎ

1. ለአነስተኛ ሥራ ተቋራጭና አማካሪ ማኅበራት የሚሰጠው ሥልጠና ይዘት በመንገድ ዘርፍ በአጠቃላይ እና በተለይ በቀበሌ ተደራሽ መንገድና በመደበኛ መንገድ ሥራ እና አነስተኛና መለስተኛ ስትራክቸሮች ግንባታ ስራ ላይ የባለሙያዎችን ክህሎት በሚገነቡ ሙያዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይገለጻል፡፡
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማኅበሩ አባላት የሚሰጡት ስልጠናዎች በዋናነት በክልሉ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ በኩል የሚሰጥ ሲሆን መንገድ ልማትና ትራንፖርት ቢሮ በቅርበት መከታተልና እንደ አስፈላጊነቱ አሰልጣኝ ሊያመቻች ይችላል፡፡

qajeelsaano qineessa dandiitanno.

**8. Borreessamate Amanyoote**

1. Tenne wodho garinni pirogiraamete beqqaano ikkitanno ogeeyye borreessishsha assinannihu Qoqqowu Loosu Kaayyo Kalaqate, Industiretenna Interpirayzete Biiro widoonni ikkanno.
2. Tenne wodho garinni loosu maamarinni tantaname borreesamate umisinni woy gaamotenni shiqqanno ogeeyyera assinanni borreessishshi borreessaanchu bisi loosu hoogginore ikkansa badate assanno gari faajjenna baalunkura tuqanno doogoni assinani woshshatto garinni ikkanno.

**9. Loosu Rosichi Taje Haa'nanni Gara**

Hasiisanno garinni halaalaanchimmansa buunxoonniti ayee mootimmate uurrinshanni ikko hallanshu uurrinshanni dagganno loosu rosichi taje haa'nannire ikkitanno. Ikkollana insa insawa assitanno heewo ikka hoogguro xibbuunni uynanni gumi dihee'ranno.

**10. Borreessamate Ikkado Ikka Hooga**

Ayno Olluu tuqishshi doogo ijaarsinna hattono madawanya doogo manaadonna mereerima isitiraakicherubba ijaarsira beqqitanno kontirakiterenna amaalaancho maamarra borreessate shiqqino ku'laato borreessamate ikkado ikkitannokkihu:

1. Miillate rosu qixxaawo woy loosu rosichi

**8. የአመዘጋገብ ሥርዓት**

1. በዚህ ደንብ መሠረት ለፕሮግራሙ ተሳታፊ የሚሆኑ ባለሙያዎች ምዝገባ የሚከናወነው በክልሉ ሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ኢንዱስትሪና ኢንተርፕራይዝ ቢሮ ይሆናል፡፡
2. በዚህ ደንብ መሰረት በማኀበርነት ተደራጅተው ለመመዝገብ በተናጠል ወይም በቡድን ለሚቀርቡ ባለሙያዎች የሚደረገው ምዝገባ መዝጋቢው አካል በሚያደርገው ስራ አጥ መሆናቸዉ ልየታ ግልጽና ለሁሉም ተደራሽ በሆነ መንገድ በሚደረግ ጥሪ መሠረት ይሆናል፡፡

**9. የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት**

እንደ አስፈላጊነቱ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ ማንኛውም ከመንግስት ተቋማትም ሆነ ከግሉ ዘርፍ የሚመጡ የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡፡ ሆኖም ለእርስ በእርስ ውድድር ካልሆነ በስተቀር በመቶኛ የሚሰጥ ዋጋ አይኖረውም፡፡

**10. ለምዝገባ ብቁ ያለመሆን**

ማንኛውም በቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ እንዲሁም በመደበኛ መንገድ አነስተኛና መለስተኛ ስትራክቸሮች ግንባታ ላይ የሚሳተፉ የሥራ ተቋራጭና አማካሪ ማኀበራትን ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ ለምዝገባ ብቁ የማይሆንባቸው ሁኔታዎች፡-

1. የአባላቱ የትምህርት ዝግጅት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማታለል ተግባር ወይም

taje awaawuratenni woy kaphunni afi'noonnita ikkase buuxanturo;

2. Wolu mootimmate loosi aana noore ikkansa buunxiro;
3. Tini wodho xa'mitanno bikaancho wonshannokkiha ikkinota buunxiro maamaru borreessamate ku'laato haa'nannita dikkitanno.

**11. Doora/Filate Amanyoote**

1. Wodhi-woro
   a) Tenne wodhota hooffaaydi bikaancho wonshitino ogeeyye taalo heewisamate qoosso heedhannonsa.
   b) Konni cinaanchu quwira fidale (a) hunda worroonnihu noo gedeenni hee'reenna meyaati balaxate kaayyo horaameette ikkitanno.
   c) Pirogiraamete beqqate hassaato noonsa ogeeyye kiiro hasi'nannihu aleenni ikkituro doorshu rosu qixxaawonni woyyaawino rosu deerri noosihu balaxo afi'ranno.
   d) Kontirakiterimmatenna amaaalaanchimmate maamarinni tantanatannore doorate tittirshu doorshu bikaanchi hajo la'annosi bisinni fulanno.

2. Jeefishsha
   a) Borreessanno bisi doorshu bikaanchi garinni borreessantino ogeeyye shiqishshino taje buuxatenninna bikaancho wonshitinore heewisiisatenni doorate looso

በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

2. በሌላ በመንግስት ስራ ላይ ያሉ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. ይህ ደንብ የሚጠይቀውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ የማህበሩ የምዝገባ ማመልከቻ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**11. የምልመላ/የመረጣ ሥርዓት**

1. መርሆዎች
   ሀ)የዚህን ደንብ ዝቅተኛውን መስፈርት ያሟሉ ባለሙያዎች እኩል የተወዳደሪነት መብት ይኖራቸዋል፡፡
   ለ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሴቶች የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡
   ሐ) በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ባለሙያዎች ቁጥር ከሚፈለገው በላይ ከሆነ ምርጫው በትምህርት ዝግጅት አንፃር የተሻለ ትምህርት ደረጃ ያለው ቅድሚያ ያገኛል፡፡
   መ)በተቋራጭነትና በአማካሪነት ማኅበር የሚደራጁትን ለመመልመል ዝርዝር የመመልመያ መስፈርት በሚመለከተው አካል ይወጣል፡፡

2. አፈጻጸም
   ሀ) መዝጋቢው አካል በመምረጫ መስፈርቶቹ መሠረት የተመዘገቡ ባለሙያዎች ያቀረቧቸውን ሰነዶች በማጣራት እና

loosanno.

b) Ogeeyyete fajjo kaima assatenni maamaru miilla waaxo lae maamarunnihanna miillate beehache wonsanno, hattono maamarunniha badooshshu su’ma borreessanno.

c) Doorshu loosi goofiro borreessi bisi heewisamaanote guma loosu base hooweranna borreessate ha’rinsho beqqaano ikkitino loosu minna hoowe giddo faajete leellanno baycho xalla woy xallamanno gede assa noosi.

d) Doorshu ledo xaadinohunni koffeenyu noonsa ku’laano koffeenyansa heewote gumi egensiishshunni faajje assine xallini barri aane noo barrinni hanafe kiiramano 5/ontu/ loosu barri giddo tenne wodhora quwa 20 hundaanni worroonni komitera shiqisha dandiitanno.

## 12. Borreessishshunna Tajete Woraqata Aate Gara

1. Tenne wodho quwa 11 cinaancho quwa 2 garinni dooramino maamarira tajete woraqata uynannihu:

   a) Miilla wo’manti hajo la’annosi bisinni uynanni qajeelsha adhansa buunxiro;

   b) Maamaru garisinni daddalu loossa borreessaanno bisinni fajjo afi’riro;

   c) Loosu Kaayyo Kalaqate, Industiretenna Interpirayzete Biironni loosu kaayyo lainohunni garumma noonsa miilla maamaraho beeqitinore ikkansa xawisanno

መስፈርቶቹን ያሟሉትን በማወዳደር የመምረጥ ሥራ ያከናውናል፡፡

ለ) የባለሙያዎቹን ፈቃደኝነት መሠረት በማድረግ የማኅበሩን አባላት ስብጥር አይቶ የማኅበሩንና የአባላቱን ድልድል ያፀድቃል፣ እንዲሁም የማኅበሩን መለያ ስያሜም ይመዘግባል፡፡

ሐ) የመረጣው ሥራ ሲጠናቀቅ መዝጋቢው አካል የተወዳዳሪዎችን ውጤት በመሥሪያ ቤቱ ግቢና በምዝገባው ሂደት ተሳታፊ በነበሩ መ/ቤቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ በግልጽ በሚታይ ሥፍራ መለጠፍ ወይም እንዲለጠፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

መ) ከመረጣው ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያላቸው አመልካቾች ቅሬታቸውን ውጤቱ በማስታወቂያ በይፋ ከተለጠፈበት ቀን ማግስት ጀምሮ በሚቆጠሩ 5 /አምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 ሥር ለተመለከተው ኮሚቴ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

## 12. የምዝገባና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለተመረጠው ማኅበር የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

   ሀ) አባላቱ በሙሉ በሚመለከተው አካል የሚሰጠውን ሥልጠና መውሰዳቸው ሲረጋገጥ፤

   ለ) ማኅበሩ አግባብ ባለው የንግድ ሥራዎች መዝጋቢ አካል የንግድ ፈቃድ ሲያገኝ፤

taje uyroti.

2. Kontirakiterimmatenna amaalaanchimmate maamari ogimmate fajjo woy deerra aate gara konstiraakishiinete biilloonyinni gumullanniha ikkanno.
3. Borreessamate taje lekkishshunni aa didandiinanni.

**13. Ogimmate Akatoommenna Woloota Wodho Ayirrisa**

Ayee maamarinna maamaru miilla hojjinni ikko mitteenni uytanno owaante xa'mitanno akatoommenna owaante aate e'anno sheemaate, hattono woloota loosu ledo xaadooshshu noonsa wodho, biddisuwana jeeffishshu maanuwaalubba ayirrisate gadacho noonsa.

## GAFA SASE

## <u>Kontirakiterimmate woy Amaalaanchimmate Maamarranni Loosantanno pirojekitubbanna Assinanni Irkonna Ha'ruunso</u>

**14. Pirojekitete Bikka**

1. Tenne wodho garinni tantanamanno kontirakiterimmate maamarira dirunni uynanni doogote ijaarsano ikko care iillishate loosi bikki mereerimunni 15km-30km geeshsha iillanno dizaaynetena doogote ijaarsi

ሐ) ከሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ኢንዱስትሪና ኢንተርፕራይዞች ቢሮ ከሥራ ዕድል አንጻር አግባብነት ያላቸው አባላት በማህበር የተሳተፉ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ሲሰጥ ይሆናል።

2. የሥራ ተቋራጭነትና የአማካሪነት ማኅበር የሙያ ፈቃድ ወይም ደረጃ አሰጣጥ በኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የሚወሰን ይሆናል።
3. የምዝገባ ምስክር ወረቀት በውክልና ሊሰጥ አይችልም።

**13. የሙያ ሥነ ምግባርና ሌሎች ደንቦችን ስለማክበር**

ማንኛውም ማኅበርና የማኅበሩ አባላት በነጠላና በጋራ የሚሰጡት አገልግሎት የሚጠይቀውን ሥነ ምግባርና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚፈጽሙትን ውል፣ እንዲሁም ሌሎች ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸውን ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአፈጻጸም ማኑዋሎች የማክበር ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል ሦስት

## <u>በሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበራት ስለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እና ስለሚደረግ ድጋፍና ክትትል</u>

**14. የፕሮጀክት መጠን**

1. በዚህ ደንብ መሠረት ለሚደራጀው የሥራ ተቋራጭ ማኅበር በዓመት የሚሰጥ የመንገድ ግንባታም ሆነ ጠጠር ማመላለስ ሥራ መጠን በአማካይ ከ15 እስከ 30 ኪ.ሜ. የሚደርስ

superivizhiinete loosa uynanniha ikkanno.

2. Tenne wodho garinni tantanamanno loosu amalaanchi maamarira dirunni uynannihu loosu bikki mereerimunni 60km-80km seendilli noonsa pirojekitubba ikkitanna amaalaanchu loosino qayyasa, dizaynenna sheemaatu gashshoote hattono xaphooma isilanchimma qorqorshi looso ikkanno.
3. Konni quwi cinaanchu quwi 1 nna 2 hundaanni worroonniri noo gedeenni hee’renna uynanni loosi bikki pirojekitootu akati injonna hasiishshi garinni lexxara woy ajara dandaanno.

**15. Ledote Pirojekitubba**

Mittu manaadu kontirakiterichi woy amaalaanchi aleenni fajjinoonnita diru pirojekite bikka 75 xibbunninna hakkuy aleenni garunni gumuliro ledote albaani fajinoonnisi pirojekite geeshshita adhara dandaanno. Ikkollana tittirshu pirojekitete loosu jeefishshi keeno qoqqowu ogeeyyenni assine Biirote gumulshu hedo shiqqeenna wonsineenna jeefinsanniha ikkanno.

**16. Ha’runso**

1. Kontirakiterimmate woy amalaanchimmate maamari barru barrunnita loosu millimmo ha’runsatenni irkisatenna qorqorate looso qoqqowunni kayse woradu geeshsha doogotenna hodhishshu tantanonni assinanniha ikkanna loosu millimmo ha’runsatenni irkonna qorqorshu looso qarunni woradu doogotenna

የዲዛይንና የመንገድ ግንባታ ሱፐርቪዥን ስራ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

2. በዚህ ደንብ መሠረት ለሚደራጀው የሥራ አማካሪ ማኅበር በዓመት የሚሰጥ የሥራ መጠን በአማካይ ከ60 እስከ 80 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው ፕሮጀክቶች ሲሆኑ የአማካሪው ሥራ ቅየሳ፣ ዲዛይን እና ኮንትራት አስተዳደር እንዲሁም አጠቃላይ የጥራት ቁጥጥር ሥራ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የሚሰጠው የሥራ መጠን እንደ ፕሮጀክቶቹ ሁኔታ ምቹነትና አስፈላጊነት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

**15. ተጨማሪ ፕሮጀክቶች**

አንድ የአነስተኛ ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ከላይ የተፈቀደውን ዓመታዊ የፕሮጀክት መጠን 75 ከመቶ እና ከዛ በላይ በአግባቡ ካጠናቀቀ ተጨማሪ ቀደም ሲል የተፈቀደውን የፕሮጀክት መጠን ያህል ለመውሰድ ይችላል፡፡ ይሁንና ዝርዝር የፕሮጀክቱ ሥራ አፈጻጸም ግምገማ በክልሉ ባለሙያዎች ተከናውኖ ለቢሮው የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ ሲጸድቅ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**16. ክትትል**

1. የሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበር የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸውን እየተከታተለ የመደገፍና የመቆጣጠር ተግባር ከክልል እስከ ወረዳ ባለው የመንገዶችና ትራንስፖርት መዋቅር የሚፈጸም ሲሆን

hodhishshu latishshi borro mini loosanoha ikkanno.

2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 aana worroonnihu noo gedeenni hee'renna madawanya doogote loosi millimmo ha'runsatenni irkonna qorqorsha assate looso qoqqowuni kayse woradu geeshsha doogote tantano woy distirikite loossannoha ikkanno.
3. Loosu amaalaanchi pirogiraametenni, isilanchimmatenninna wolootu kontiraatu gashshooti ledo xaaddino qarrubba leeltanno loosu muraano aana borrote qorowonni kayse sheemaate diigate iillishshanno qaafo adhate dandiisiisannota wo'ma taje loosiisi'ranno loosi miniranna qorqoranno loosu minira shiqisha hasiissannosi.
4. Kontirakiterimmate woy amaalaanchimmate maamarranni loosantinoti akatoommete xe'ne lowohunni luphi yituro loosiisi'rannohu laonni woy gumulonni muishshu, awaawurshu, wolqate assootubba sheematu jeefishshi ha'rinisho aana iillishshino yee ammaniro hattono dhuku aleenni ikkino gadachanno korkaati nookkiha maamaru owaantesi bade woy wo'muni wo'ma 60 (leya) ajjannokki barrubbanni shiqisha woy ijaarsu looso loosa hoogiro woradu doogotenna hodhishshu latishshi borro mini hattono distirikitete shiqqanno taje garinni Biiro hajote aana amaalantenna gumulo saysatenni konne borreessino bisira egensiisatenni tajete

የየዕለት የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸውን እየተከታተሉ የመደገፍና የመቆጣጠር ተግባር በዋናነት በወረዳ መንገድ ልማትና ትራንስፖርት ጽ/ቤት የሚከናወን ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የመደበኛ መንገዶች የስራ እንቅስቃሴ እየተከታተለ የመደገፍና የመቆጣጠር ተግባር ከክልል እስከ ወረዳ ባለው የመንገዶች መዋቅር ወይም ዲስትሪክት የሚከናወን ይሆናል፡፡
3. የሥራ አማካሪው ከመርሃ ግብር፣ ከጥራት እና ሌሎች ከኮንትራት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ችግሮች በሚታዩባቸው የሥራ ተቋራጮች ላይ ከጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ውል ማቋረጥ የሚያደርስ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የተሟላ መረጃ ለአሰሪው መስሪያ ቤትና ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
4. በሥራ ተቋራጮች ወይም አማካሪ ማኅበራት የተፈፀመው የሥነ ምግባር ጥሰት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ በአሰሪው ዕይታ ወይም ውሳኔ የሙስና፣ የማጭበርበር፣ የሀይል ተግባራት በውሉ አፈጻጸም ሂደት ላይ ፈጽመዋል ብሎ ካመነ እንዲሁም ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ በለሌበት ማኅበሩ አገልግሎቱን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከ60 (ስልሳ) ለማያንሱ ቀናቶች ካላቀረበ ወይም ግንባታውን ካላከናወነ የወረዳው መንገድ ልማትና ትራንስፖርት ጽ/ቤት እንዲሁም ዲስትሪክቶች በሚቀርበው መረጃ መሰረት ቢሮው በጉዳዩ ላይ በመምከርና ውሳኔ በማስተላለፍ ይህንኑ ለመዝጋቢው አካል

woraqata rigidanno gede xa’ma dandiitanno..

**17. Borreessishshu Taje Rigida**

1. Tenne wodho garinni kontirakitere woy amaalaanchu maamarira uynoonnisi taje rigindannihu:
    a) Kontirakitere maamari woy amaalaanchu maamari taalotu ali miilla aye korkaatinni loosu aana leellate dandiisannosikki/dandiisiisannosakki korkaati xaadiro;
    b) Miillanniti rosu qixxaawo woy loosu gade taje awaawurshunni woy kaphunni afi’noonnita ikkase buunxiro;
    c) Maamaru miilla giddonni loosa dandiisannokkihu mannimmate woy surrete gawajjo noosiha ikkeenna maamaru bobbahino looso gumaamo diassanno yine ammannanniha ikkiro woy maamaru tini wodho xa’mitannoha woloota bikaano wonshinokkiha ikke leelliro;
    d) Aye doogonni tajete woraqata wolootu horonsidhanno gede sayse aa buunxiro;
    e) Garu noo wolu seerinni maamaru tajete woraqati woy miillannihu ogimmate ikkadimma buuxo taje rigidantanno gede gumulliro borreessino bisinni rigidantara dandiitanno.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 fidale (a) hunda xawinsoonni korkaatinni tajete woraqati rigidamino maamari miili wirro wole ogeeyye

በማሳወቅ የምስክር ወረቀቱ እንዲሰረዝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**17. የምዝገባ የምስክር ወረቀትን ስለመሰረዝ**

1. በዚህ ደንብ መሰረት ለሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበሩ የተሰጠው የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚሰረዘው፡-
    ሀ) ለሥራ ተቋራጩ ማኅበር ወይም ለሥራ አማካሪው ማኅበር ከግማሽ በላይ አባላት በማናቸውም ምክንያት በሥራው ላይ ለመገኘት የማያስችለው/ላቸው ምክንያት ሲያጋጥም፤
    ለ) የአባላቱ የትምህርት ዝግጅት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማታለል ተግባር ወይም በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
    ሐ) ከማኅበሩ አባላት መካከል መስራት የማያስችለው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለበት በመሆኑ ማኅበሩ የሚሰማራበትን ሥራ ውጤታማ አያደርገውም ተብሎ የሚታመን ሲሆን ወይም ማኅበሩ ይህ ደንብ የሚጠይቀውን ሌሎች መስፈርቶችንም ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ፤
    መ) በማናቸውም መንገድ የምስክር ወረቀቱ ለሌሎች መጠቀሚያ እንዲሆን ተላልፎ መሰጠቱ ሲረጋገጥ፤
    ሠ) አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የማኅበሩ የምስክር ወረቀት ወይም የአባላቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰረዝ ሲወሰን በመዝጋቢው አካል ሊሰረዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ (ሀ) በተገለፀው ምክንያት የምስክር ወረቀቱ

ledo maamarra tantane maamara borreesiisa didandaanno.

3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 iima woroonnnihu heerirono miilu mittu manchi gede isi umisi maamaru diigamara doogimale assooti noosikkiha ikkiro biirotenni woy hajo la'annonsa bissanni gumulliro wirro maamarunni tantanamanna borreessama dandaanno.
4. Miilu konni quwi cinaanchu quwi 3 garinni owaatamara dandaannohu maamaru miilla xe'ne mittu aganinni roortinokki yanna giddo tenne egensiise maamarunniha tajete woraqata qolinoha ikkiro, woy maamaru amadino pirojekitubba gooffa geeshsha angasi keeshshishanno gede borreessino bisinni fajjo uynoonnisiha ikkirooti.

## 18. Borreessantino Fajjo Ittisa

1. Tenne wodho quwa 13 tittirroonni bikaano wonsheenna borreessamate taje uynoonnisi maamari tajete woraqata afi'ri gedensaanni loosu jeefishshi ledo xaadinohunni luphi yitino disippiliinete xe'ne loosasira qummeessu woy woxaratto shiqquro borreessino bisi maamaru yinoonni huno loosasi buunxa geeshsha uynoonnisi taje mitto agana sa'inokki yannara ittisara dandaanno.
2. Borreessino bisinni tajete woraqati ittisamanno gede assinoonni maamari woy maamaru miilla aana shiqqino huno buuxe mittu agani giddo gumulo aa noosi.

የተሰረዘበት ማኀበር አባል እንደገና ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር ማኀበር አደራጅቶ ማኀበሩን ማስመዝገብ አይችልም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ቢኖርም አባሉ እንደ አንድ ግለሰብ በማኀበሩ መበተን አሉታዊ አስተዋጽኦ ከሌለው በቢሮው ወይም በሚመለከተው አካል ከተወሰነ እንደገና መደራጀትና ማስመዝገብ ይችላል፡፡
4. አባሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ሊስተናገድ የሚችለው የማኀበሩን አባላት መኀደል ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይህንኑ አሳውቆ የማኀበሩን የምስክር ወረቀት መልሶ እንደሆነ፣ ወይም በማኀበሩ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ በእጁ እንዲያቆየው ከመዝጋቢው አካል ፈቃድ የተሰጠው እንደሆነ ነው፡፡

## 18. የምዝገባ ፈቃድ ስለማገድ

1. በዚህ ድንብ አንቀጽ 13 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ማኀበር የምስክር ወረቀቱን ካገኘ በኋላ ከሥራ አፈጻጸም ጋር በተገናኘ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ወይም አቤቱታ በጽሁፍ ሲቀርብ መዝጋቢው አካል ማኀበሩ የተነገረበትን ጥፋት ስለመፈፀሙ እስኪጣራ ድረስ የተሰጠውን የምስክር ወረቀት ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያግደው ይችላል፡፡
2. መዝጋቢው አካል የምስክር ወረቀቱ እንዲታገድ በተደረገ ማኀበር ወይም የማኀበር አባል ላይ የቀረበውን ጥፋት አጣርቶ በአንድ

3. Borreessino bisi tenne yanna giddo fajjote rigida, ittisote ka"a woy wole gumulo aatenni tenneno hajote annira borrotenni aa woy loosu mini giddo xawo ikkino bayicho xalla noosi.
4. Ittishshu yanna giddo gumulo uynoonnikkiha ikkiro tini yanna gooffuro ayee maamaru miili shiqishi'ranno ku'laato koffeenya macciishshitanno komite ittishshu hakkawoytenni ka"anno gede gumultanno.

5. Konni quwi cinaancho quwi 1 garinni ittishsha uynoonni maamari disippiliinete hajo qoqqowoho hajo la'annosi bisinni la"amannoha ikke leelliro borreessino bisi tenne ittishshu yanna giddo hajo haja la'annosi bisira soaa noosi.
6. Konni quwi cinaanchu quwi 1 garinni uynanni ittishshi aana woxaratto dishiqqanno.
7. Maamaru fajjo quwa 17 cinaancho quwa 1 fidale (b) garinni rigidamanno gede gumulliro hunaanchu seerunni xa'mamanno gede haja la'annosi bisira sa"a noosi.
8. Konni quwi cinaanchu quwi 1 woroonnihu noo gedeenni hee'reenna mittu agani giddo buuxxanno bisi sufona woy sufoonke yitanno gumulo afi'ra hoogiro loosiisi'ranohu loosu mini pirojekite wole kontirakiterera aara dandaanno.

ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3. መዝጋቢው አካል በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለፈቃዱ መሰረዝ፣ ስለ ዕገዳው መነሳት ወይም ሌላ ውሳኔ በመስጠት ይህንን ለባለጉዳዩ በጽሁፍ መስጠት ወይም በመሥሪያ ቤቱ በግልጽ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡
4. በዕገዳው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠ እንደሆነ ይህ ጊዜ ሲጠናቀቅ ማንኛውም የማኅበሩ አባል በሚያቀርበው ማመልከቻ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ዕገዳው ወዲያውኑ እንዲነሳ ይወሰናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 መሠረት ዕገዳ የተሰጠበት ማኅበር የዲሲፕሊን ጉዳይ በክልሉ አግባብ ባለው አካል የሚታይ ሆኖ ሲገኝ መዝጋቢው አካል በዚሁ የዕገዳ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል መላክ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 መሠረት በሚሰጥ ዕገዳ ላይ አቤቱታ አይቀርብበትም፡፡
7. የማኅበሩ ፈቃድ በአንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ መሠረት እንዲሰረዝ ሲወሰን ጥፋተኛው በሕግ እንዲጠየቅ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል መተላለፍ አለበት፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚያጣራው አካል ይቀጥል ወይም አይቀጥል የሚል ውሳኔ ካላገኘ አሰሪው መስሪያ ቤት ፕሮጀክቱን ለሌላ ሥራ ተቋራጭ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**19. Yannannita Taje aa**

Borreessino bisi aye yannarano kontirakiterete woy amaalaanchu aana adhinoonni qaafonna uynoonni gumulo ha'runse haja la'annonsa bissara yannanita taje aate gadacho noosi.

## GAFA SHOOLE

## Koffeenya Shiqishate Amanyoote

**20. Woxaratto Shiqishi'ra**

1. Kontirakiterimmate heewisame dooraminokkihu woy disippiliinetenni woy wolu korkaatinni uynoonnisihu tajete woraqati rigidamanno gede borreessino bisinni gumulloonnisihu woy tenne wodho quwa 18 cinaancho quwa 2 hunda worroonni garinni ittishshu ka"annosi gede xa'mi'rano ku'laanchi borreessino bisi uyno gumulo aana tenne wodho quwa 21 garinni uurritanno komitera gumulo woy ittishshu gara ikkinokki korkaata xawisatenni woxaratto shiqishi'rara dandaanno.
2. Ku'laanchu komitete koffeenyasi shiqishi'ra dandaannohu dorama hoogasi kullihunni woy rigidamanno gede borreessino bisinni gumulo faajjetenni uyni barri soodihunni kayse kiirranni 5 (ontu) loosu barri giddo ikkanno.
3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 hunda worroonni yanna giddo hajote gumulo uynoonnikkihu woy ittishsha kayinsoonnisikki ku'laanchi konni quwi cinaanchu quwi 2 hunda

**19. ወቅታዊ መረጃ ስለመስጠት**

መዝጋቢው አካል በማንኛውም ጊዜ በሥራ ተቋራጩ ወይም አማካሪው ላይ የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተሰጡ ውሳኔዎችን እየተከታተለ ለሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

**20. አቤቱታ ስለማቅረብ**

1. ለሥራ ተቋራጭነት ተወዳድሮ ያልተመረጠ ወይም በዲሲፕሊን ወይም በሌላ ምክንያት የተሰጠው የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በመዝጋቢው አካል የተወሰነበት ወይም በዚህ ደንብ በአንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው ሁኔታ ዕገዳው እንዲነሳለት የሚጠይቅ አመልካች መዝጋቢው አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ ደንብ አንቀጽ 21 መሠረት ለሚቋቋመው ኮሚቴ ውሳኔው ወይም ዕገዳው አግባብ ያልሆነበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. አመልካች ለኮሚቴው ቅሬታውን ማቅረብ የሚችለው አለመመረጡ ከተገለፀበት ወይም እንዲሰረዝ በመዝጋቢው አካል ውሳኔ በይፋ ከተሰጠበት ቀን ማግስት ጀምሮ በሚቆጠር 5 (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለጉዳዩ ውሳኔ ያልተሰጠው ወይም ዕገዳ ያልተነሳለት አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳይገታ በማንኛውም ጊዜ ጥያቄውን

worrooni yanna hooltusikkinni aye yannarano xa’mosi koffeenya macciishshitanno komitera shiqishi’ra dandaanno.

**21. Qaranna Tekinikete Komite Uuurra, Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Xaphooma pirogiraamete loossa aliidimatenni harunsitanno qara komite hattono tittirishi pirogiraamete loossa harunsitanno tekinikete komite tenne wodhonni uurritino.
2. Qara komite batinyenna kariso jeefisiisaanote amaale mini gumulannoha ikkanna konni woroonni noo biilloonyinna loosu qeechi heerannose.
   a) Tekinikete komite aliidimmatenni massagganno.
   b) Uurrinshunni bocu boci dirinninna hasiisiro hakkiinni ajjino yannanni gambooshshe assitanno.
   c) Fillanni bikaancho fushshitanno; woyyeessitanno.
   d) Tekinikete komitenni loosantanno loosa keentanno; woyyeessate hedo shiqishshanno; wonsitanno.
   e) Mitu kontirakiteremmate woy amaalaanchimmate maamari aye korkaatinni doorama hoogasinni woy ku’laanchu tajubba haara hoogatenni sa’anno gumulo aana shiqqanno koffeenyubba la’annota mereerima koffeenya macciishshate komite uurissanno.

ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**21. የአብይ እና ቴክኒክ ኮሚቴ መቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር**

1. አጠቃላይ የፕሮግራሙን ሥራዎች በበላይነት የሚከታተል አቢይ ኮሚቴ እና ዝርዝር የፕሮግራሙን ተግባራት የሚከታተል የቴክኒክ ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. የአቢይ ኮሚቴ አባላት ብዛት እና ስብጥር በመስተዳድር ምክር ቤት የሚወሰን ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከተ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡
   ሀ) የቴክኒክ ኮሚቴን በበላይነት ይመራል፤
   ለ) በቋሚነት በየሩብ ዓመቱና እንደ አስፈላጊነቱም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ስብሰባ ያካሂዳል፤
   ሐ) የምልመላ መስፈርት ያወጣል፤ያሻሽላል፤
   መ) በቴክኒክ ኮሚቴ የሚከናወኑ ሥራዎችን ይገመግማል፤ የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፤ ያጸድቃል፤
   ሠ) አንድ የሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ማኅበር በማናቸውም ምክንያት ባለመመረጡ ወይም የአመልካቹን ማስረጃዎች ባለመቀበል በሚተላለፈው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚያይ ገለልተኛ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፤
   ረ) የሥራ ተቋራጩ ወይም አማካሪው ማኅበር በምዝገባው ወቅት በሚፈፅመው የዲሲፒሊን ጉድለት ከምዝገባው

f) Kontiratitere woy amaalaanchu maamari borreessamate yannara assanno disippiliinete xe'ne borreessamate wiinni rigidamanno gede borreessino bisinni gumulliro shiqino koffeenyi garinni uynoonni gumulo ka'anno, kaajjitanno woy wirro la"antanno gede assitanno.

3. Tekinikete Komite Loosu qeechinna Sooreessimma Tekinikete komite qara komite giddo noo loosu minnanni fultinore 5 (onte) ogeeyye amaddinotanna tekinikete looso loossannota ikkite:
   a) Worroonni borreessamate safaraanchi garinni amaalaanonna kontirakitere maamarra borreessate looso loossanno;
   b) Worroonni filate safaraanchi garinni borreessantino maamarra filtanno; doortanno;
   c) Filate/doorate gumi rippoorte yannatenni qara komitera shiqishshanno; gumulsiissanno; gumulono borreessamaanote egensiissanno;
   d) Woloota qara komitenni uynanniha ledote loossa loossanno.

## 22. Hoolloonni Assoote

1. Ayno tenne wodho garinni tajete woraqatisi ittisaminohu woy tajete woraqatasi rigindonni kontirakitere woy amaalaanchi tajete woraqatisi ittisame hee'reenna woy rigidame noo yanna giddo borreessino bisinni baxxino

እንዲሰረዝ በመዝጋቢው አካል ሲወሰን በቀረበው ቅሬታ መሰረት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳ፣ እንዲፀና ወይም እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፡፡

3. የቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት
   የቴክኒክ ኮሚቴው በአብይ ኮሚቴ ውስጥ ከተካተቱት መ/ቤቶች የተውጣጡ 5 (አምስት) ባለሙያዎችን የያዘና የቴክኒክ ሥራዎችን የሚሰራ ይሆናል፡፡
   ሀ) በተቀመጠው የምዝገባ መስፈርት መሰረት የአማካሪና የተቋራጭ ማኅበራትን ምዝገባ ያከናውናል፡፡
   ለ) በተቀመጠው የምልመላ መስፈርት መሰረት የተመዘገቡ ማኅበራትን ይመለምላል፤ ይመርጣል፡፡
   ሐ) የምልመላውን/የመረጣውን ውጤት ሪፖርት በወቅቱ ለአብይ ኮሚቴው ያቀርባል፤ ያስወስናል፤ ውሳኔውንም ለተመዝጋቢዎች ያሳውቃል፡፡
   መ) ሌሎች በአብይ ኮሚቴ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 22. ክልከላ

1. ማንኛውም በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የምስክር ወረቀቱ የታገደበት ወይም የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ የምስክር ወረቀቱ ታግዶ ባለበት ወይም ተሰርዞ ባለበት ጊዜ ውስጥ ከመዝጋቢው አካል በልዩ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ መሰረት የተፈቀዱ ሥራዎችን ሊያከናውን አይችልም፡፡

garinni shiima yannara keeshshitanno fajjo aa hoongisiro tenne wodho garinni fajjinoonni loosa loosara didandaanno.

2. Borreessanno bisinni tajete woraqata rigindonni woy ittinsoonnisi kontirakiterichi woy amaalaanchi tajete woraqatisi rigidame woy ittisame noo yannara tenne wodho garinni uynoonnisita ikkadimmate buuxo horonsi're fushshi'rino daddalu fajjonni horonsi'ra didandaanno.

**GAFA ONTE**

**Addi Addi Woro**

**23. Halamate Gadacho**

Ayeno hajo la'annonsa bissa tenne wodho jeefishshira halamate gadacho noonsa.

**24. Jeefishshu Nookki Seerinna Assooti**

Tenne wodho ledo kiphi yaano seerinna rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubbara jeefishshu dinonsa.

**25. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Tenne wodho loosu iima hosiisate hasiisanno biddissa biiro fushshitara dandiitanno.

**26. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho Badheessa 20/2013 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

2. በመዝጋቢው አካል የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ወይም የታገደበት የሥራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ የምስክር ወረቀቱ ተሰርዞ ወይም ታግዶ ባለበት ወቅት በዚህ ደንብ መሠረት በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ተመርኩዞ ባወጣው የንግድ ፈቃድ መገልገል አይችልም፡፡

**ክፍል አምስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**23. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ለደንቡ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**24. ተፈጻሚነት የሌላ ሕግና አሰራር**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ሕግና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

**25. መመሪያን የማውጣት ስልጣን**

ይህን ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ መመሪያ ቢሮው ሊያወጣ ይችላል፡፡

**26. ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመጋቢት ፳ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

**Hawaasa, Badheessa 20, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

**ሀዋሳ፣ መጋቢት ፳ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**

# Amadisinsonni

**Shae 1**

**Olluu Tuqishshi Doogo Ijaarsi Loosi Aana Bobbahanno Manaadu Kontirakitere Maamari**

| A.K | Loosu sooreessima | Rosunna Qajeelishshu dani | Garumma Noosi Loosu Rosichi Dirunni | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Digire | Dipilooma | Levele 4 na aleeni | sertifikkeete |
| 1 | Loosu harisaancho | Sivil injineeringetenna labbanno ogimmanni qajeelinohu (doogo ijaarsate) | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | Uduunu qoqqorqoraanchi /Material Engineer/ | Sivil injineeringetenna injineeringete jiolojjeni (Uduunu eo qorqoraanchi) | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | Stirakicherete dizayine, ijaarsunna isilaanchima qorqoraancho | Sivil injineeringete, jiolojjete, haydirolikkisete, hoydirolojete | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | Superi atendaante/ konstiraakishinete formaane | Konisitiraakishinete tekinoloje manajimente doogo ijaarsatena gatamarate loosi | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | Qeyyaashe | Qiyyesu loosini /Surveying/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | Shallagote Ogeessa /Accountant/ | Akkawuntinge, Akkawuntingenna faynaanse, Ikonomikse | 0 | 0 | 0 | 0 |

**Shae 2**

## Manaadanna Mereerima Istiraakicherubba Ijaarsatenna Chare Hodhisate Looso Loosanno Maamara

| A.K | Loosu sooreessima | Rosunna Qajeelishshu dani | Garumma Noosi Loosu Rosichi Dirunni | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Digire | Dipilooma | Levele 4 na aleeni | sertifikkeete |
| 1 | Loosu harisaancho | Sivil injineeringe, konistrakishiinete tekinolojenna labbanno ogimma handaarinni | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | Uduunu qoqqorqoraanchi/ Material Engineer/ | Sivil injineeringe, jiolojjete injineeringenni /Uduunu eo qoqqorqoraanchi/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | Stirakicherete dizayine, ijaarsunna isilaanchima qorqoraancho | Sivil injineeringe, jiolojjete injineeringenni haydirolikise, haydirolojikal injineeringete | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | Superi intendante/ konstiraakishiinete formaane/ | Konisitiraakishinete tekinoloje manajimente doogo ijaarsatena gatamarate loosi digire, dipilooma leveli 4 ikkiro ‘COC’ noosihu/nooseti | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | Qeyyaashe | Qiyyesu loosini/Surveying/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | Shallagote Ogeessa /Accountant/ | Akkawuntinge, Akkawuntingenna faynaanse, Ikonomikse | 0 | 0 | 0 | 0 |

**Shae 3**

## Manaada Istiraakicherubba Ijaarsate Aanana Chare Doogote Iilishshate Loosira Bobbakkano Manaada Loosu Muraano Maamara

| A.K | Loosu sooreessima | Rosunna Qajeelishshu dani | Garumma Noosi Loosu Rosichi Dirunni | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Digire | Dipilooma | Levele 4 na aleeni | sertifikkeete |
| 1 | Loosu harisaancho | Sivil Injineeringetenna, labanno oggimani gajeelinohu (Doogo ijaarsate) | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | Uduunu eo qoqqorqoraanchi /Material Engineer/ | Sivil Injineeringete, konistirakshin manajimetetenni, haywoy injineeringe, jiolojikal injineeringetenna labbanno ogimmate handaari | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | Qeyyaashe | Qiyyesu loosini/ Surveying/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | Hayidirolojjiste | Hayidirolikkisete, Hayidirolojjetena labbano oggimani | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | Qarqaru agarooshshi ogeessa | Invayromentaale injineeringe | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | Shallagote Ogeessa /Accountant/ | Akkawuntinge, Akkawuntingenna faynaanse, Ikonomikse | 0 | 0 | 0 | 0 |

# አባሪ

## ሠንጠረዥ 1

## የቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ ላይ የሚሰማራ አነስተኛ ሥራ ተቋራጭ ማኅበር

| ተ.ቁ | የሥራ ኃላፊነት | የትምህርትና ስልጠና መስክ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ በዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዲግሪ | ዲፕሎማ | ሰርተፊኬት | Level 4 እና ከዚያ በላይ |
| 1 | ሥራ አስኪያጅ | ሲቪል ምህንድስና በተመሳሳይ ሞያ የሰለጠነ /መንገድ ግንባታ/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | ግብዓት ተቆጣጣሪ /Material Engineer/ | ሲቪል ምህንድስና በኢንጅነርንግ ጅኦሎጂ/የግብዓት ተቆጣጣሪ/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | የስትራክቸር ዲዛይን፣ ግንባታ እና ጥራት ተቆጣጣሪ | ሲቪል ምህንድስና በኢንጂነሪንግ፣ ጅኦሎጂ ሀይድሮሊክስ፣ ሀይድሮሎጂ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | ሱፐር ኢንቴንዳንት /ኮንስትራክሽን ፎርማን/ | ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት መንገድ ግንባታና ጥገና ሥራ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | ቀያሽ | በቅየሳ ሥራ (surveying) | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | የሒሳብ ባለሞያ | በአካውንትንግ፣ በኢኮኖሚክስ ዲግሪ ያለው/ያላት | 0 | 0 | 0 | 0 |

## ሠንጠረዥ 2

### የአነስተኛ መለስተኛ ስትራክቸር ግንባታ እና የጠጠር ማመላለስ ሥራ ላይ የሚሰማራ ማኅበር

| ተ.ቁ | የሥራ ኃላፊነት | የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ በዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዲግሪ | ዲፕሎማ | ሰርተፊኬት | Level 4 እና ከዚያ በላይ |
| 1 | ሥራ አስኪያጅ | በሲቪል ምህንድስና፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | ግብዓት ተቆጣጣሪ /Material Engineer/ | ሲቪል ምህንድስና፣ በጅኦሎጂካል ኢንጂነሪንግ /የግብዓት ተቆጣጣሪ/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | የስትራክቸር ዲዛይን፣ ግንባታ እና ጥራት ተቆጣጣሪ | ሲቪል ምህንድስና፣ ጂኦሎጂካል ኢንጂነሪንግ፣ ሀይድሮሊክስ፣ ሀይድሮሎጂካል ኢንጂነሪንግ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | ሱፐር ኢንቴንዳንት /ኮንስትራክሽን ፎርማን/ | ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት መንገድ ግንባታና ጥገና ሥራ ዲግሪ ዲፕሎማ ለቢል Level 4 ከሆነ COC ያለው ያላት | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | ቀያሽ | በቅየሳ ሥራ (surveying) | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | የሒሳብ ባለሞያ | በአካውንትንግ፣ በኢኮኖሚክስ ዲግሪ ያለው/ያላት | 0 | 0 | 0 | 0 |

## ሠንጠረዥ 3

## የአነስተኛ ሥራ አማካሪ ማኅበር

| ተ.ቁ | የሥራ ኃላፊነት | የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ በዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዲግሪ | ዲፕሎማ | ሰርተፊኬት | Level 4 እና ከዚያ በላይ |
| 1 | ሥራ አስኪያጅ | ሲቪል ምህንድስና እና ተዛማጅ ሙያ የሰለጠነ /መንገድ ግንባታ/ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | ግብዓት ተቆጣጣሪ /Material Engineer/ | ሲቪል ምህንድስና፣ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ ሃይ ወይ ኢንጂነሪንግ፣ ጂኦሎጂካል ኢንጂነሪንግና በተመሳሳይ ሞያ ዘርፍ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | ቀያሽ | በቅየሳ ሥራ (surveying) | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | ሀይድሮሎጂስት | በሀይድሮሊክስ፣ በሀይድሮሎጂ እና በተመሳሳይ ሞያ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | የአከባቢ ጥበቃ ባለሞያ/ | ኢንቫይሮመንታል ኢንጂነሪንግ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | የሒሳብ ሠራተኛ | አካውንትንግ፣ ኢኮኖሚክስና ማኔጅመንት ዲግሪ ያለው/ያላት | 0 | 0 | 0 | 0 |